EthioLion

# “ይድረስ ‘ለአገር ዳኛ’ ”

የጐንቻው!

ሳር ቅጠሉ፤ ገመድ ተፍተለተለና፤
ሽምቀቅ ማተብ ሆነ፤እምነቱ፤ቀረና፤
በላይን ሰቀሉት፤የላቀውን ጀግና፤
ማነቆ አደባባይ፤የትውልድ ገመና፤
ከጠላት ባዳናት፤በአገሩ፤መዲና፤
ስቅላት ውለታው፤እርግምት ነውና፤
ብርክ መዳህ ጀመርን ነፃነት፤ልመና፤
በላይ እምቢ ብሎ አኛ እጅ ሰጠንና፤
ያውም ከባዕድ አገር ተሰፍሮ፤በቁና፤
ይድረስ፤ለአገር ዳኛው፤ሕዝቡ በደፈና፤
ዛሬም ከዳታችን፤አልተፋቀምና፤
**ስንት ‘በላይ’ ሰቅለን እንሰይም ጐዳና።**

በዘመነ ንጉሥ፤‘ግርማሜ’፤ሲሞት፤
አገር ሳይቆጣ፤ሳይተጋ፤ወጣት፤
በዘመነ ‘ደርግም’፤ስንቱ፤ዜጋ፤እልፈት፤
ጥቂቶች፤ሲተጉ፤መንጋው ሲራኮት፤
የባሰ፤ደንቀራ፤ተጋረጠበት፤
ዘመነ፤ወያኔ፤መከራ፤ግዞት፤
**አገር-ሕዝብ፤የሚያሥር፤በዘር ሰንሰለት።**

ሕዝብ የሚያስጨርስ ነፍሰ-በላ፤ዳኛ፤
ለምን አይጠየቅ፤በአገር አደባባይ፤ችሎት ‘መስቀልኛ’፤
ሁነኛ ሰው ጠፍቶ፤ጠበቃ፤የሚሆን፤ አዋቂ ቁርጠኛ፤
‘እድሜ፤ልክ’ እሥራት፤ ተፈረደ ‘በእኛ’፤
ይድረስ ለአገር ሸንጐ፤ይድረስ ለአገር ዳኛ፤
ለምን ፍትህ አትሰጥ፤ይግባኝ የማይሽረው፤አሳሪና እስረኛ፤
ብይን አስቆጭተህ፤እጥር ምጥን ያለ፤‘ሰውኛ-አገርኛ’፤
**አትደግስም ወይ፤በቀናት፤በወራት፤ወያኔን መሸኛ።**

በፍርሃት ማዕበል፤አገር ሲጥለቀለቅ፤
በክህደት፤ጐርፍ ምጣት፤ሰው ከቀየው ሲለቅ፤
እንባ ባዘነበው፤ደም በቋጠረው፤ ሃይቅ፤
በወያኔ አዞዎች፤በቁም ሰው፤ሲቦጨቅ፤
ገመና እሚሸፍን፤ሱሪ፤የሚያስታጥቅ፤
በአገር ጀግና ሲነጥፍ፤ወንዙ፤ምንጩ፤ሲደርቅ፤
ጓዳ እሚያወላዳ፤ቀሚስም እሚያጠልቅ፤
ቅርጣን የተረፉ፤ቃል፤የጠበቁ፤ሃቅ፤
የ’ግርማሜን’ መንፈስ፤የበላይን ሰንደቅ፤
እንቁ የአበሻ፤ልጆች፤የትውልድ ፈርጥ ወርቅ፤
ስማቸው፤አርማቸው፤በአለም የሚደነቅ፤
ማተብ ይሁን አልቦ ካቴናቸው፤ይውለቅ፤
ይድረስ ለአገር ዳኛው፤አፎት፤እንዲታጠቅ፤
**አሳሪው ይታሰር፤ክህደቱ፤ይሸምቀቅ።**

በአኬልዳም ሸብር፤የተፈረጁት፤
‘ጥፋት’ ባጋለጡ፤እስር ስቅላት፤
*<u>አንዷለም፤እሥክንድር፤ጀግናዋ ርዕዮት፤</u>*
*<u>ዘመኑ፤በቀለ፤ናትናዔል፤አሳምን፤ደግሞም፤ውብሸት፤</u>*
ከሺህ ተቆራኝተው፤ስለ ሕዝብ፤ስለ አገር የተሳሰሩት፤
ለዓለም መቀጣጫ፤ንብረት ነፍስ፤አራጣ፤የሚገብሩት፤
ይድረስ የአገር ዳኛ፤ዋስም ጠበቃ ሁን፤ውጣና ታገት፤
አበሳችን ይሻር፤ሰይም አደባባይ፤የእምነት የምህረት፤
ሕዝብ ሸንጐ፤ጠርቶ፤የብይን ችሎት፤
ይፍረድ፤ የአገር ዳኛ፤በቀን በወራት፤
ታሳሪ፤አሳሪውን፤እንዲጠይቁት፤
**በአገር ‘መስቀልኛ’፤እንዲያፋጥጡት።**

yegonchaw@hyahoo.co.uk

## በእስራትና በቅጣት፤ለሚንገላቱ፤ብርቅ ድንቅ ኢትዮጵያዊያን ድጋፍ፡-

- በውስብስብ ታሪካችን፤ውድ ሕይዎታቸውን መስዋዕትነት ከፍለው፤እንደ አንድ ሰው፤እንደ ዜጋ፤ ሰብዓዊ ክብር፤ጻጋ፤ኩራት፤ማንነት አጐናጽፈውን ያለፍ፤ኢትዮጵያዊያን ቁጥር በጣም ግዙፍ ነው፤ ይኸንን ጀግንነታቸውን መስዋዕትነታቸውን በአብዛኛው ስንዘክር ኖረናል።
- ይሁንና በተለይ፤በዚህ በቅርቡ ‘በኛ ዘመን’ ለጊዜውም ቢሆን ‘ደመ-ከልብ’ያደረግናቸው፤ እስኪሚያሰኝ፤ የረሳናቸው ወይም የሞቱለትን ዓላማ ችላ ያልነውና ከሕዝቡ፤ አእምሮ የደበዘዙም፤ይመስላሉ። ኃያው ጀብዱ፤ ሰርተው ያለፉ፤ እህት ወንድሞቻችን፤ ወላጆቻቸው እንባ ሳይታበስ፤ ሃዘናቸውን በውስጣቸው ቀብረው፤ በተስፋ የሚኖሩ ወገኖቻችን በጣም ብዙ ናቸው።
- አሁንም የወያኔ መንግሥት፤ ስለገመተን፤ስለናቀን፤ በሽብር አሳቦ፤ቁጥር ስፍር የሌላቸውን፤ ወገኖቻችንን፤ ብርቅዬ መሪዎቻችን፤ የላቁ፤ ባለሞያዎቻችንን፤ ጋዜጠኞቻችንን፤በእስራት፤ስቅላት፤ ሲያንገላታ፤ሲያሰቃያቸው፤ከንፈር እየመጠጥን፤በየጓዳው፤ቡና የምናቃርር፤ወሬ፤የምናመንዝክ፤ ሞልተናል።
- እንደዚህ በቀላሉ፤ ለእውነት፤የቆሙ፤እህት ወንድሞቻችንን አሳልፈን የምንሰጥ ከሆነ፤ፍጹም ነፃነት የማይገባን ሕዝቦች ነን፤ከዚህ በኋላ፤በትውልድም፤በታሪክም፤ተጠያቂዎች፤የለየለት የጠላት፤ድቃላ፤ወያኔ ብቻ ሳይሆን፤ ዝምተኛው፤ ‘ሰማኒያ ሚሊዮን’ ሕዝብ ጭምር ነው።
- በዚይ የሚገርም የታሪክ አጋጣሚ፤ዘመነኞች፤ ደባ-ደራማ፤ በአደባባይ፤እያቀነባበሩ፤ሲያቀርቡልን፤በቁጣ እንኳ፤’ድንጋይ የወረወረ፤አመጹን በሥራ ማቆም አድማ የገለፀ’ የለም። ከዚህ በላይ ምን ሊመጣ ነው? መቼ ነው ሕዝብ የሚቆጣው?
- ከአብራኩ የወጡ፤እህት ወንድሞቹን፤ልጆቹን፤ወላጆቹትን፤ እድሜ ልክ ሲያስሩበት፤ሞት፤ስቅላት፤ሲፈርዱባቸው፤ሳይዋደቅ፤ዝም ብሎ ካዬ፤ የዚህ ዓይነት ሕዝብና አገር፤ወገንም፤ዜጋም መሆን፤አልሻም።

Ethiopia Will Prevail!